# ነፃነት ራዲዮ ምን ነካዉ?

**ጌታቸዉ ረዳ**

ትናንት ማታ የነፃነት ራዲዮ ሳዳምጥ፤ የዕለቱ እንግዳ አድርገዉ ያቀረቡዋቸዉ የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ምክትል ሊቀመንበር የሆኑት ክቡር አቶ አባይነህ ብርሃኑ ነበሩ። ታዲያ በጋዜጠኞቹ በኩል በቃለመጠይቁ የቀረቡት ጥያቄዎችም ሆኑ ለእንግዳዉም ለድርጅቱም ያሳዩት ከበሬታ በጣም የወረደ ከአንጋፋ ጋዜጠኞች እና በትግሉ ላይ ብዙ ዓመታት የቆዩ እና ከተካኑ ከተማሩ ሰዎች የሚጠበቅ ሆኖ አላገኙሁትም።

በዚህ ሁለት ሳምንት አለመታደል ሆኖ የምወደዉና በአማርኛዉ የጽሁፍ ያቀራረብ ዉበቱ የማደንቀዉ ራዲዮን ሳልጠብቀዉ በብዙ ሁኔታዎች በስሜት እተጠመደ እንዳሳዘነኝ፤ ጥልቅ ሂጀ ራዲዮኑን ለመተቸት ባልፈለግሁበት ምክንያት ላይ ላዩን በጥቄት ሐረጎች ባለፈዉ ሳምንት ተችቼዉ እንዳለፍኩት ታስታዉሳላችሁ።

ትናንት (ዕሁድ) ደግሞ ከተከበሩ አቶ አባይነህ ጋር ዉይይት ሲያደርግ ከማናናቅ እሰከ ቀኖናዊ ክርክር ዉስጥ ከእንግዳዉ ጋር አታካራ ሲገባ ማዳመጤ እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ አሳዝኖኛል።

ራዲዮኑ ባለፈዉ ሰሞን ከ አድማጭ የተላከ ጽሁፍ በሚል ያቀረቡት እኔን ያስገረመኝ ጉዳይ ወደ ጎን ልተዉና፤ በኣቶ አባይነህ ብርሃኑ ላይ እና በመኢአድ ላይ የተወረወረዉ ትግሉን የማናናቅ ባሕሪ ሲቀርብ እንደጋዜጠኛ ሳይሆን የቀረበዉ ከማወቅ ወይንም ትግሉን ካለመረዳት ከስሜት የተነሳ የመኢአድን ትግል ለማንኳሰስ የቀረበ የሚመስል አቀራረብ ተደምጧል። እርግጠኛ ነኝ ጋዜጠኞቹ መልካም አገር ወዳድ ዜጎች መሆናቸዉን አልክድም፡ ሆኖም፡ የራዲዮኑ አዘጋጆች እንግዳዉን ምን ምን መጠቅ እንደነበረባቸዉ የተዘጋጁ አይመስሉም። ቢዘጋጁም፤ ያቀረቡዋቸዉ ጥያቄዎች በሕዝቡ ጆሮ ምን-እንደምታ-ያስከትላል-ብለዉ አልተነጋገሩባቸዉም ይመስላሉ።

መኢአድ አምስት ሚሊዮን አባል አለን ካለ ኢትዮጵያን በመግዛት ላይ ያለዉ የትግራይ ነፃ አዉጭ ድርጅት አራት ሚሊዮን አባሎች አሉኝ ይላል፡ -መኢአድ በቁጥር ከወያኔዉ አባል ይበልጣል እና  ልምን የወያኔ ፈቃድ ትጠብቃላችሁ? በማለት አቶ አባይነህ ብርሃኑን ከበሰሉ ጋዜጠኞች የማይጠበቅ ዕዉቀት ሳይሆን ስሜት የነዳዉ ጥያቄ ማንሳቱ እጅግ አስጋረሚ ሆኖ ካገኘሁት አንዱ ይሂኛዉ ጥያቅያቸዉ ነበር።

እንግዳዉ ደጋግመዉ በወያኔ ምሕረትና እጅ የምንንቀሳቀስ እና አስተንፈሱ ስንባል የምናስተነፍስ አታስተንፍሱ ሲለን የማናስተነፍስ ‘ወያኔ ሰራሽ ዕቃ” ሳንሆን ራሱን ጠብቆ ሕዝቡን የትግሉን መሪ እና ተዋናይ እያደረገ፤ እየሞተ፤ እየታሰረ እየተጋዘ፤ እየተዋረደ እየታረዘ፤ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሲያግደንም ድኳን ተክለን፤ አትሰበሰቡ ሲለን የመሰብሰብ መብታችነን እናስከብራለን ብሎ አሻፈረኝ ስላለ እተገደለ ደምፁን እያስከበረ ነዉ...” የሚል መልስ ሲያገኙም “አታካራ እና ስሜት የከሸነዉ ቀኖና ዉስጥ በመግባት የማናናቅ ወይንም “እየዋሻችሁን ነዉ” የሚያስመስለዉ አባባል ዓይነቱ ንትረክ ገብተዉ ማድመጤ በጣም እጅግ በጣም ገርሞኛል።

ለማንኛዉም እንግዳዉ በቂ እና አኩሪ መረጃ ስለሰጡ በጣም ረክቻለሁ። ሰሞኑን በሚቀጥለዉ ቀሪ የቃለ ምልልሱ ክፍለ ጊዜ ጋዜጠኞቹ ተዘጋጅተዉ ከስሜት ወጥተዉ ከነባራዊዉ ዓለም ጋር የሚገናኝ ጥያቄ አዘጋጅተዉ ተሻሽለዉ እንደሚቀርቡ ተስፋ እያደረግሁ እንደ ዕሁዱ ክፈለጊዜያቸዉ ዕዉር ድምብሩን እንዳያስኬዱት ምጥኔታየ የላቀ ነዉ። //--//

www.ethiopiansemay.blogspot.com